# <u>የኢሮብ ታሪክ ጥያቄዎችና አባባሎች</u>

ከግርማይ ተስፋገርጊስ

ክፍል ሶስት

በክፍል አንድና ሁለት የኢሮብ ቅድመ-አያቶች የትውልድ ሐረጎችን በሚመለከት የተፃፉ ልዩልዩ ጽሑፎችን ምንም ዓይነት አስተያየት ወይም ትችት ሳይደረግበት እንዳለ ለማሳየት ተሞክሯል። ፅሑፎቹ የቀረቡበት መሠረታዊ ዓላማም የኢሮብ ህዝብ አመጣጥን አስመልክተው የተፃፉ የተለያዩ አፈ-ታሪኮች መኖራቸውን በማሳየት፣ የታሪክ ጠበብትን የኢሮብ ህዝብ ታሪካዊ አመጣጥ ለመመርመርና ለማጥናት ሊያነሳሳ ይችላል ከሚል እሳቤ ነው። ትክክለኛ የኢሮብ ህዝብ ታሪክ እንዲጻፍ ከተፈለገ በትውፊት የሚነገሩና በፅሑፍ የሠፈሩ ታሪኮችን በማገናዘብ መመራመር እንደሚያስፈልግ የሚያጠያይቅ አይሆንም። በተለይ ባለንበት በሃያ-አንደኛው ክፍለ-ዘመን። በመሆኑም፤ ትውፊቶችም ሆኑ በፅሑፍ የሰፈሩ ታሪኮችና አፈ-ታሪኮች ሳይጣመሙ በፅሑፍ ሰፍረው ለትውልድ ቢተላለፉ ለምርምር ጥሩ መነሻ ሊሆኑ እንደሚችሉ አያጠራጥርም። ስለሆነም፤ ባህላችንና ቋንቋችንን ሳናጠፋ፤ ትውፊቶችን ይዘን አፈ-ታሪኮችን መመርመር አስፈላጊ ይሆናል። ይህንን አካሄድ ተከትለን የተገኙትን ታሪኮችና አፈ-ታሪኮችን ሳይዛቡ እንዳሉ ከተቀመጡ ባሁኑ ጊዜ ይህንን ለመተግበር ብቃት ያላቸው የተማሩ የኢሮብ ወጣቶች በተለያዩ ክፍለ-ዓለማት መኖራቸው ጋር ተዳምሮ ሲታይ የኢሮብ ህዝብ አመጣጥ ታሪክ ላይ ለመመራመር ጊዜው አመች የሚሆን ይመስላል። የትምህርት ዕድል ያላገኙ አያቶችና ቅድመ-አያቶች በቃል ያስተላለፉትን ማጣራትና ከተቻለ አጣርቶ በጽሑፍ ማስተላለፍ ተገቢ ነው። አንድ አፈ-ታሪክ እውነተኛ ከሆነ እውነተኛነቱን የሚደግፉ ምንጮችን መፈለግ፣ እውነት የማይመስል ነገር ካለበት ደግሞ ለምን እውነት ሊሆን እንደማይችል ምርምር ማድረግ የግድም አስፈላጊም ነው። በዚህ መጣጥፍ ክፍል ሁለት የተፃፈውን ያየ አንድ አንባቢ ከአባቶቻችን የተላለፈልን ታሪክ እያለን ለምንድነው ሌሎች ስለኛ የሚሉትን የምታመጣው? ከአባቶቻችን የተላለፈልንን ታሪክ አታምነውም ወይ? በማለት ጥያቄ አቅርቦልኛል። ጉዳዩ የማመንና ያለማመን ጉዳይ ሳይሆን፤ እውነቱን የማግኘት ፍላጎትና ተነሳሽነት ነው። ሆኖም፤ ከላይ እንደተገለጸው ከአባቶቻችን ለሚተላለፉልን ቁምነገሮችና እሱን እንዳለ በጽሑፍ መዝግበው ለሚያስተላልፉ ወገኖቻችን ከፍ ያለ አክበሮት እንዳለኝ በዚህ አጋጣሚ ግልጽ ማድረግ እፈልጋለሁ። ይህንን የማደርገው ነገሮችን እንዳሉ በጭፍን ተቀብለን እንዳለ በማሰተላለፍ ፈንታ ማጥናትና መመራመር አስፈላጊ መሆኑን ለማሳየትና ለማሳሰብም ጭምር ብቻ ነው።

በአፈ-ታሪክ የሚተላለፉ ተረቶች እውነት ወይም በእውነት ላይ የተመሠረቱ ሊሆኑ ይችላሉ። ሆኖም ግን ከትውልድ ወደ ትውልድ በአፍ የተተረከ ሁሉ እንደ እውነተኛ ታሪክ መወሰድ የለበትም ብዬ አምናለሁ። ምክንያቱም ለብዙ ዘመናት ሲወርድ-ሲዋረድ ከአፍ ወደ አፍ በቃል በተላለፈ ትውፊት ውስጥ ብዙ በኋላ የተጨመሩ ወይም የተረሱ ነገሮች ሊኖሩ ይችላሉ፤ የባሰ ደግሞ ሆን ተብሎ ራስን ወደ ጥሩ ነገር ወይም ጥሩ የሚመስልህ ነገር በማዛመድ ለመከበር ሲባል የሚደረጉ ለውጦች ሊኖሩ ይችላሉ። ለምሳሌ እሥራኤላውያን በአምላክ የተመረጡ ስለሆኑ በነሱ የዘር ሐረግ ውስጥ ራስህን ለማስገባት ሲባል፣ መሓመድ ነቢይ የአምላክ መልእክተኛ ስለሆነ እንደምንም የዘር ሐረግህን እሱ ጋር ለማገናኘት፣ እንዲሁም ንጉሥ ሰሎሞንና ንግሥት ሳባ በጣም ዝነኛ ስለነበሩ የነሱ የዘር ሐረግ አለኝ ለማለት ወዘተ. የተደረጉ ለውጦች ሊኖሩ ይችላሉ ብሎ መገመት ክፋት የለውም።

ሌላ ነገር ደግሞ አብዛኛው ጊዜ ታሪክ የሚባለው በጊዜው በተመዘገበ ጽሑፍ፣ በአርኬዮሎጂ ወይም በሌላ መሠረት የተደገፈ መሆን አለበት። ለምሳሌ በጥንታዊ የኢትዮጵያ ታሪክ ስማቸው የተጠቀሱ

ነገሥታትን ስንመለከት የአንዳንዶቹ መኖር በዘመነ ንግሥናቸው ጊዜ የተፃፈ ዜና-መዋዕል በማግኘት፣ በዘመናቸው በተሠራ ገንዘብ ላይ የተቀረፀ ስማቸው ወይም ስእላቸው በማግኘት ወዘተ. በእውነት የነበሩ ነገሥታት መሆናቸውን እናውቃለን። በአራተኛው ክፍለ ዘመን የአክሱም ንጉሥ የነበረው ኤዛና ለዚህ ጥሩ ምሳሌ ሊሆን ይችላል። ስለ አንዳንዶቹ በአገሪቷ ታሪክ ስማቸው የተጠቀሰ ሆኖም ግን በእውነት ስለመኖራቸው የሚያረጋግጥ ምንም ዓይነት ማስረጃ ያልተገኘላቸው አይታጡም። ለምሳሌ ቀዳማዊ ምንሊክ የሚባል ንጉሥ ነግሦ እንደነበረ የሚያረጋገጥ ማስረጃ በበኩሌ አላየሁም። ከዚህ አንጻር ሲታይ ኤዛና የሚባል ንጉሥ በአራተኛ ክፍለ ዘመን በአክሱም ነግሦ እንደነበረ የሚተረከው ትክክለኛ ታሪክ ሲሆን ቀዳማዊ ምንሊክ የሚባል ንጉሥ ነግሦ ነበረ የተባለው ግን ተረት (Legend) ይባላል ማለት ነው። ሌሎችም ብዙ ስማቸው በታሪክ የተጠቀሰ በእውነት ስለመኖራቸው ግን ምንም ዓይነት ምልክት ወይም ማስረጃ ያልተገኘላቸው አሉ። ስለዚህ ታሪክና ተረት መደባለቅ የለባቸውም። በተረት የተላለፈውን ሁሉ እንደ እውነተኛ ታሪክ የምናምን ከሆነ ዘንዶ የነገሠበት ወቅት ነበረ ተብሎ የሚተረከውንም እንደ ታሪክ ልንቀበል ነው ማለት ነውን?

ሆኖም እላይ በተጠቀሱ መለኪያዎች የተረጋገጡ ባይሆኑም እንደ ታሪክ ተቀባይነት ያላቸው አፈ-ታሪኮች ሊኖሩ ይችላሉ። ዋናው እዚህ ለማስተላለፍ የተፈለገው ቁምነገር አፈ-ታሪክን ዝም ብሎ እንዳለ በመቀበል ፈንታ እውነተኛ የመሆን ዕድሉ ምን ያህል እንደሆነ በምርምር ላይ የተመሠረተ ሚዛናዊ ግምት መስጠት ያስፈልጋል ለማለት እንጂ በአፈ-ታሪክ የሚተላለፉትን ቸል ማለት አለብን ለማለት አይደለም። እንዲያውም ከቅድመ-አያቶች ሲወርድ-ሲዋረድ ለሚተላለፉልን ተረቶች ሆነ ሌላ ቁም ነገሮች ከፍተኛ ግምት መስጠትና ተገቢ ግንዛቤ መውሰድ ያስፈልጋል።

አንድ ሕብረተሰብ የራሱ የሆነ ተረት፣ ልምድ፣ ባህልና ወግ ይኖረዋል። እነዚህ ተረቶችንና አጠቃላይ የቅድመ-አያቶች ቅርሶችን ማክበርና ለቀጣዩ ትውልድ ማስተላለፍ የግድ ያስፈልጋል። ይሁንና ታሪክንና ተረትን ለይቶ ማየት ያስፈልጋል። ስለሆነም እዚህ ለማለት የተፈለገው የሕብረተሰባችን ተረቶች፣ ባህልና ልምዶችን እያከበርን ስለ ታሪካችን በምርምርና በጥናት ላይ የተመሠረተ ዕውቀት እንዲኖረን የተቻለንን ጥረት ሁሉ እንድናደርግ ለማሳሰብ እንደሆነ ለአንባቢዎቹ ግልጽ መሆን አለበት። ተረትና ታሪክ ጎን-ለጎን ሊሄዱ ይችላሉ። ለምሳሌ ጋይሶላ ገና ሕፃን እያለ በጠላቶች ከተጣለበት አንስታ ሰስ በወተቷ አሳደገችው የሚል ተረት እየተረክን መቀጠል የሚከለክለን የለም። የሌሎች ምሳሌም ብንወስድ፤ ሮማውያን የሮማ ከተማን እስካሁን ድረስ ሮሙሉስንና ረሙስን በምታጠባ ተኵላ ሃውልቶች አስጊጧት የለም? ይህ ግን ተረታቸው (myth) እንጂ ታሪካቸው አይደለም።

ወደ ራሳችን አፈ-ታሪኮች እንመለስና በተላለፈልን አፈ-ታሪክ ውስጥ እውነተኛ ሊሆኑ ይችላሉ የምንላቸውና ለእውነተኝነታቸው ያለው ዕድል የተወሰነ ነው ወይም አሻሚ ነው የምንላቸውን ተንትነን ለመለየት መሞከር ያለብን ይመስለኛል። ስለ ኢሮብ ህዝብ መሠረተ-ትውልድና ጥንታዊ ምንጭ አስመልክቶ የተነገሩትን የተለያዩ አፈ-ታሪኮችን ስንመለከት እውነት ነው ብለን ለመቀበል በጣም አስቸጋሪ የሆኑ አባባሎችን እናገኛለን። ከነዚህም ውስጥ ለምሳሌ የኢሮብ ህዝብ ከአውሮጳ ስለመጣ ኢሮብ የሚል ስያሜ ተሰጠታል የሚል አባባልን መቀበል በብዙ መልኩ አስቸጋሪ ይመስለኛል። በተለይ ደግሞ ከታቦተ ጽዮን/የሙሴ ጽላት አመጣጥ ጋር ተያይዞ ሲቀርብ። የሙሴ ጽላት ወደ ኢትዮጵያ መምጣቱን አስመልክተው የተለያዩ ተመራማሪዎች የተለያየ እድምታ ሰጥቷል። ከነዚህ አባባሎች ውስጥ ጽላቱን ይዞ የመጣው የእሥራኤል ንጉሥ ነበረ የተባለው የሰሎሞንና የኢትዮጵያ ንግሥት ነበረች የተባለችው የሳባ ልጅ ቀዳማዊ ምንሊክ ነው የሚለው

አንዱ ነው። የኢሮብ ቅድመ-አያት ነው የተባለው እንድርያስ ወደ ኢትዮጵያ የመጣም ያኔ ነው ተብሏል። እና እስቲ ይህንን እንደ ተጨባጭ እውነት ለመቀበል ያለውን አስቸጋሪነት እንይ፦

የንጉሥ ሰሎሞን መዲና ነበረች የተባለችው ኢየሩሳሌም የምትገኘው በአውሮጳ ውስጥ ስላልሆነች እንድሪያስ ከዛ ስለመጣ ነው የሱ የልጅ-ልጆች ኢሮብ የተባሉት ሊባል አይቻልም ብለን እንለፈው። የእንድሪያስ አባት - መግድር - ሮማዊ ነበረ (ያውም የሮማ ንጉሥ) ተብሏል። በዛን ጊዜ (ከክርስቶስ ልደት በፊት 1000 ዓመት ገደማ ማለት ነው) በዚህ ስም የሚታወቅ የሮማ ንጉሥ ስለ መኖሩ የሚጠቅስ ታሪክ የለም ብቻ ሳይሆን ራሳቸው ሮማውያን እንደሚሉት ከሆነ ያኔ ከነጭራሹ ሮማ የሚባል አገር ወይም ከተማ አልነበረም። የነሱ ተረት ሮማ የተመሠረተችው ከክርስቶስ ልደት በፊት በ750 ገደማ ሮሙሉስና ረሙስ በሚባሉ ተኵላ ያሳደገቻቸው መንትየ ሁለት ወንድማሞች ነው። ሮማ የሚባል ስም የወጣላትም ከነዚህ መጀመርያ አቋቋሙዋት ከሚባሉ መንትዮዎች ባንደኛው (ሮሙሉስ) ስም ነው። ታዲያ ሮማ ሳትመሠረት እንዴት ብሎ ነው - ሮማ የሚል ስም ያለው አገር ወይም መንደር ከነጭራሹ ሳይኖር - መግድር የሚባል የሮማ ንጉሥ ሊኖር የሚችለው? ይህ የሚያመለክተው ተረቱ እውነት ላይ የተመሠረተ እንዳልሆነ ነው። በሮማ ስለ ነገሡ ነገሥታት ታሪክ መናገር የሚቻለው ከክርስቶስ ልደት በፊት ከ500 አካባቢ በኋላ ነው። ታዲያ የኢሮብ ህዝብ ቅድመ-አያት እንድሪያስ የሮማ ንጉሥ መግድርና የእሥራኤሉ የንጉሥ ዳዊት ልጅ የሆነችው የንግሥት ኢለኒ ልጅ ነበረ፣ ወደ ኢትዮጵያ የመጣውም ደግሞ የእሥራኤሉ ንጉሥ ሰሎሞንና የኢትዮጵያ ንግሥት ሳባ ልጅ ነበረ የተባለው ቀዳማዊ ምንሊክ ጽላተ-ሙሴን ይዞ ወደ አክሱም የመጣበት ጊዜ ጽላቷን አጅበው ከመጡት ጋር ነው የሚል ብሂል እውነት ሊሆን የሚችል ይመስላል? እንድሪያስ መሠረቱ ከሮማ ነው የሚባለው እውነት ቢሆን እንኳ በዛን ዘመን በአህጉር ራስህን ማስተዋወቅ የተለመደ ነገር ነበርን? ያኔ ከሮማ የመጣ ሮማዊ ነኝ፣ ከግሪክ የመጣ ግርካዊ ነኝ ከማለት በላይ የመሄድ ልምድ ሊኖር የሚችል አይመስለኝም። እሱም በጊዜአቸው በጣም የሰለጠኑ ከሆኑ ነው። ካልሆነ ግን አተናዊ፣ ስፓርታዊ ወዘተ. ማለት ሊቀላቸው ይችላል። አንድ ሰው በዛን ዘመን መሠረቱ ከዛ አከባቢ ስለ ሆነ ወደ ሌላ አህጉር ሲሄድ ራሱን አውሮጳዊ ነኝ ብሎ ያስተዋውቅ ነበረ የሚል ብሂል ቢያንስ አጠያያቂ ነው እንበለው።ስለዚህ የኢሮብ ህዝብ ቅድመ-አያት ምንጭና መሠረት ሮማና እሥራኤል ነው የሚል እና ህዝቡ ከአውሮጳ ስለመጣ ኢሮብ ተባለ የሚለው አፈ-ታሪክ መመርመር ያለበት ይሆናል።

ሁለተኛ አባባል ለዮ ራይንሽ የተባለ ኦስትርያዊ ምሁር የፃፈው ነው። ፀሓፊው ኢሮብና ሌሎች የኢሮብ አጎራባች የሆኑ የሳሆ ቋንቋ ተናጋሪ ጎሳዎች የኢሮብ ህዝብ ከግሪክ የመጣ ዘር ነው ብለው እንደሚያምኑ ስለዚህም ኢሮብ እንደተባሉ ነው የመዘገበው። የኸኛው አባባልስ እውነትነት ይኖረው ይሁን? የአክሱም ሥልጣኔ ከፍተኛ ደረጃ በደረሰባቸው ዘመኖች ብዙ ግሪካውያን ወደ ኢትዮጵያ ይመጡ እንደነበረ ይታወቃል። በአክሱም ከተማ የሚኖሩ ግርካውያን እንደነበሩ፣ የአክሱም መንግሥት ለውጭ ንግድ የሚጠቀምበት ገንዘብ በግእዝና ግሪክ ቋንቋ ፊደሎች ይፅፍ እንደነበረ ወዘተ. በፅሑፍና በአርከዮሎጂ የተደገፈ ታሪክ ነው። ስለዚህ በአገሪቷ የቀሩ ግርካውያን ሊኖሩ ይችላሉ። ስለዚህ ኢሮብ በዚህ መልክ የቀሩ ግርካውያን ዘር ነው የሚለው አባባል እውነት ሊሆንም ላይሆንም ይችላል። ስለዚህም መጠናት ያለበት እንጂ ፈፅሞ የማይቻል ነው ተብሎ የሚጣል አይደለም ለማለት ነው። ህዝቡ ኢሮብ የተባለው የግሪክ ዘር ስለሆነ ነው የሚል ግን እላይ በተጠቀሰው ምክንያት የማይመስል ነው።

በዚህ መጣጥፍ በክፍል ሁለት ላይ እንዳየነው፤ ፊተ. ሚካኤል ሓሳማ የኢሮብ ህዝብ እንደ ሐዶ (ሓዞ)፣ ሱሩክሶ፣ ቶርዓ ወዘተ. መዓውያ ተብለው ከሚጠሩ ዓረባዊ ዘሮች እንደሆኑ ፅፏል። ደራሲው

መዓውያ ደማስቆን መናገሻው ያደረገ የዓረብ ንጉሥ እንደነበረ፣ እሱ ከሞተ በኋላ ግን ሌላ ተቀናቃኝ ነገድ ስልጣን ይዞ የመዓውያ ዘሮችን ስለአሳደደ የመዓውያ ነገድ የሆኑት ካገራቸው ፈልሰው ቀይ ባህርን በመሻገር ወደ ምድራችን እንደመጡ ሰፋ አድርገው ዘግቧል። ቀጥሎም ኢሮብና ሌሎች ብዙ በኤርትራ፣ በትግራይና በጅቡቲ የሚኖሩ ጎሳዎች የነሱ (የመዓውያ) ዘር እንደሆኑ ጽፈዋል።

አሁን የሚነሳው ጥያቄ የኢሮብ የትውልድ ሐረግ ከመዓውያ ነው የተባለው እውነት ሊሆን ይችላል ወይ የሚለው ይሆናል። ይህም መጠናት ያለበት እንጂ እንዲሁ በስሜት ብቻ ነው ወይም ኣይደለም ተብሎ የሚደመደም አይደለም። ባጭሩ የኢሮብ ሕዝብ ከአባት ወደ አባት የመዓውያ ዘር ሊሆንም ላይሆንም ስለሚችል መጠናት ያለበት ነው ብዬ አልፈዋለሁ።

ወደ ሌሎች አባበሎች ከመግባቴ በፊት ከዚህ ጋር በተያያዘ አንድ መጠቀስ አለበት የምለውን ነጥብ አስጨብጬ ልለፍ። ሓዞና ሌሎች ፊተ. ሚካኤል የመዘገቧቸው ጎሳዎች የመዓውያ ዘር ናቸው ያሉት እውነት ቢሆን ኢሮብም አባት በኣባት ባይሆንም በሐዞ በኩል የመዓውያ የዘር ሓረግ አለበት ማለት ነው። ምክንያቱም በኢሮብ ውስጥ በሓዞ የማይወለድ ያለ አይመስለኝም። ይህም ሓዞና ኢሮብ ከጥንት ጀምረው ተመላልሰው ስለተጋቡ ነው። በኢሮብና ሓዞ መካከል የተፈፀሙ ጋብቻዊ ግኑኝነቶችን ሁሉ እዚህ መጥቀስ ባይቻልም የተወሰኑት የጥንቶቹን ልጥቀስ፦

1) ሓሳባላ መጀመርያ ዋራ የምትባል የሓዞ ተወላጅን በኋላ ደግሞ ዒሳ የምትባል የዋራ ዘመድን (ሁለቱም የሓዞ ተወላጆች መሆናቸው ነው) አግብቶ መላው ሓሳባላን ወልዷል። ስለዚህ በዚህ መልክ ሓሳባላ በሙሉ የሓዞ ተወላጆች ናቸው ማለት ነው።

2) የቡክናይታ አራተኛ ልጅ የሆነው ኣፍራሃ-በዐራ ማሊካ የምትባል የሓዞ ተወላጅን አግብቶ ከአስሚዒ-ፊረ በስተቀር መላ ቡክናይቲ-ዓረን አፈራ፤ አስሚዒ-ፊረም በኋላ ከሓዞ ጋር ተጋብቷል። ስለዚህ በቡክናይቲ-ዓረም በሓዞ የማይወለድ የለም ማለት ነው።

3) አድጋዲ-ዓረ ውስጥም የሓዞ የዘር ሓረግ የሌለው ያለ አይመሰለኝም። ለምሳሌ የብዙዎቹ የአድጋዲ-ዓረ ህዝብ ቅድመ-አያት የሆነው ኣውዓላ የሓዞ ተወላጅ የሆነችው ሥልጣናን አግብቶ ወልደገረጊስ፣ ዓንደገርጊስ፣ ሓያሎም፣ ዳቱ፣ አፍራሓና ማናን… ወልዷል። ሌሎች የአድጋዲ-ዓረ ነገዶችም እኔ ባላወቅም እንደ ሌሎች የኢሮብ ነገዶች ከሓዞ ጋር ደጋግመው ተጋብተው ሊሆኑ ይችላሉ።

ይህን የኢሮብና ሐዞ መዋለድን በሚመለከት አቶ ሚኪኤል ገብራይ የተባሉ የኢሮብ ተወላጅ በሳሆ ቋንቋ በገጠሙት አጭር ግጥም እዘጋዋለሁ።

ዮኮሊክ ቃይሲ ያም ሒነ
ዮኮሊክ ሰክቲ ያም ሒነ
ሓዲ ኣቡሳ ኪክ ኒነ
ሓዲ ኒ አቡሳ ኪክ ዪነ
ኣማይማሕ ለ መዔም ኒነ።

የግጥሙ ዋና መልእክት ከሓዞ ጋር ያለን የቆየ ዝመድናና ፍቅር በሃይማኖት ልዩነት ምክኒያት መቀነስ የለበትም ነው (የኢሮብ ህዝብ በብዛት የክርስትና ሃይማኖት ተከታይ ሲሆን ሓዶ/ሓዞ በብዛት ሙስሊም ናቸው)።

የኢሮብ ህዝብ የትውልድ መሠረትን በሚመለከት የተለያዩ አፈ-ታሪኮች እንዳሉ ከላይ ባጭሩ አይተናል። የህዝቡ የትውልድ ሓረግ ከሮማና ከእሥራኤል መሆኑን ገልፆ የህዝቡ ስያሜ ከዚህ ጋር የሚያያይዘውን አፈ-ታሪክ ለማመን አስቸጋሪ እንደሆነም በአመክንዮ በማስደገፍ ለመግለፅ ተመክሯል። ሁለተኛ የኢሮብ ህዝብ አመጣጥና ስያሜ ከአውሮጳ ጋር የሚያያይዝ አፈታሪክ በለዮ ራይንሽ የቀረበው የኢሮብ የትውልድ መሠረት ግሪክ የሚያደርግ የህዝቡ ስያሜም በዚህ ምክንየት ኢሮብ ተባለ የሚለው ነው። የህዝቡ የትውልድ መሠረት ግሪክ ነው የሚለው መጠናት ያለበት ሲሆን የህዝቡ ስያሜ ከዚህ ጋር መያያዙ ግን የማይታመን መሆኑም ተጠቅሷል። ሌላው ፊተ. ሚካኤል የመዘገቡት የኢሮብ ህዝብ ትውልድ ከዓረቡ መዓውያ ጋር የሚያያይዝ ታሪክ ነው።

ይህንን አባባል የሚደግፍ ከሌላ ምንጭ የሰማሁት ወይም በፅሑፍ ያገኘሁት ነገር የለም። አባባሉ በዚህ መጣጥፍ የተጠቀሰው ደራሲው ተረቱን የእገላ-ሓጺን አዋቂዎች የመዓውያ ዘር መሆነቸውን አጽድቀዉልኛል ስላሉ ነው። የእገላ-ሓጺን ህዝብ ከኢሮብ ጋር የተቆራኘ የዘር ሐረግ እንዳለው ደግሞ በብዙ ምንጭ የተደገፈ ነው። ስለሆነም አባባሉን የማይቻል ነው ብሎ ከመዝጋት ማጥናቱ የተሻለ ነው።

ወደ ሌላ ነጥብ ከመግባቴ በፊት ስለ እገላ-ሐጺን ህዝብ ፊተ. ሚካኤል የጻፉት የህዝቡ ልምድ ከኢሮብ ህዝብ ልምድ ጋር የሚያመሳስል ነገር ልጥቀስ፦ ፊተ. ሚካኤል እገላ-ሐጺን በማንነታቸው እጅግ በጣም የሚኮሩ ነፃነታቸውን ለማስከበር ወደኋላ የማይሉ ጅግኖች መሆናቸውን ይገልፃሉ። ደራሲው በመቀጠል ይህ ጎሳ ከጣሊያን በፊት ህዝብ ራሱ መሪውን ይመርጥ እንደነበረ መዝግቧል። ይህ ልምድ ህዝቡን ከኢሮብ ህዝብ ጋር ያመሳስሏል። ጣሊያን ኢትዮጵያን ወሮ እስከተቆጣጠረበት ጊዜ ድረስ የኢሮብ ህዝብም ለአገርቷ ከፍተኛ መሪ እውቅና ከመስጠቱ ባሻገር ውስጣዊ ነፃነቱን አስከብሮ የሚኖር መሪውን በምርጫ የሚሾም ህዝብ ነበር።

ሌላው ቱክረት ሰጥተን ልንመለከተው የሚገባን ነጥብ የኢሮብ ህዝብ የትውልድ ሐረግ ከላስታ ነገሥታት ጋር የሚያያይዘው አፈ-ታሪክን ነው። ይህ አባባል የበለጠ ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶት መመርመር ያለበት ይመስለኛል። ምክንያቱም እስካሁን ያየናቸው ተረቶች በብዛት ወደዛ የሚያመላክቱ ከመሆናቸው በተጨማሪ የኢሮብ ህዝብ የሚናገረው ቋንቋና አንዳንድ ባህላዊ ይዘቶች ከሌሎች የተጠቀሱ አገሮችና ቋንቋዎች ይበልጥ ከአገው (ላስታ) እና ሌሎች ኩሻዊ በሚል ስያሜ ከሚታወቁ ቋንቋዎችና ባህሎች ጋር ይቀራረባል።

መጀመርያ የተለያዩ ፀሐፍት ምን እንደሚሉ እስኪ እንይ፦ የኢሮብ ቅድመ-አያቶች ከዓረብ የመጡ ናቸው ያሉ ፊተ. ሚካኤል ሓሳማ ሳይቀሩ ከኢሮብ ጋር የዘር ዝምድና ያላቸው እገላ-ሓፂን፣ ሮብራ፣ ትምዛእ የመሳሰሉ በኤርትራ የሚኖሩ ጎሳዎች የላስታው የንጉሥ ይትባረክ ዘር ነን እንደሚሉ ጠቅሷል።

ጆሜትራ ገብረ ኢየሱስ አባይ ደግሞ በበኩላቸው በዓጋመ የሚኖሩ የኢሮብ ህዝብና በ፯ ገናሕቲ የሠፈሩ የትእዛዝ ዘሮች፣ እንዲሁም በተለያዩ የኤርትራ ቀበሌዎች የሚኖሩ እገላ-ሐጺን፣ እገላ-ደገብስ፣ እገላ-ሐመስ፣ ትምዘአ፣ ላምዛ፣ ዓዲ-ደጊያት አቤነር፣ ሮብራ፣ ኮርባርያ ወዘተ. የትውልድ መሠረት ላስታ እንደሆነ ከዛም የአፄ ይትባረክ ልጆች መሆናቸውን ነው የመዘገቡት።

ካርሎ ኮንቲ ሮሲኒ ‘ኣል ራጋሊ’ (Al Ragali) በተባለው መጽሓፉ በልዩ ልዩ አፈታሪኮች ውስጥ እንደምናገኘው የኢሮብ ሕዝብ ቅድመ አያቶች አሁን የኢሮብ ህዝብ ወደሚኖርበት ቦታ መጥተው ቋሚ መኖርያቸው ከማድረጋቸው በፊት ከዓፋር አከባቢ በላዓሲ-ጋደ አድርገው የጉንደጉንደ ገዳም ወዳለበት ደጋማ አከባቢ የመጡ መሆን አለባቸው ይላል። በዚህ መጣጥፍ ክፍል አንድ ውስጥ እንዳየነው አከባቢው የኢሮብ አፈታሪክ አፄ ይትባረክ ሸፍቶበት እንደነበረ የተመለከተው አከባቢ መሆኑ ነው። ይህ አፈ-ታሪክ የኢሮብ ቅድመ አያት ወረደ-ምሕረት በምን አኳኋን ከአፄ ይትባረክ እንደተወለደ ሰፋ አድርጎ ይተርካል። ተረት ሁሉ ጊዜ አንድ የራሱ የሆነ ልዩ የሚያደርገው ይዘት አለው፤ እንዲሁም አንዳንድ ከሌሎች ተረቶች ጋር የሚያመሳስሉት ብሂሎችም ይገኙበታል። ተረቱ ስለ ወረደምሕረት እናት የሚተርከው የዚሁ ተረት ልዩ መሆንን (ፓርቲኩላርቲ) ያሳያል ሊባል ይቻላል። የእጇና የእግሯ ጣቶች 24 ነበሩ የሚለው፣ ለዚህ ጠንቋይ የሰጣቸው ትርጉም፣ ወዘተ ተረቱን ልዩ የሚያደርጉ ምሳሌዎች ሊሆኑ ይችላሉ። የተወለደው ውብ ህፃን ወንዝ ውስጥ ተጣለ፣ ነጋዴዎች አግኝተዉት ወደ አለቃቸው ወሰዱት….ወዘተ የሚለው ደግሞ በተለያዩ ዘመናት በተለያዩ

ሕብረተ-ሰቦች ውስጥ ከተነገሩ ተረቶች ጋር ይመሳሰላል። ከዚህ ጋር በተያያዘ በይፋ ከሚታወቁ ተረቶች መካከል የሙሴና ከላይ የተጠቀሱ የሮሙሉስና ረሙስ ተረቶች እዚህ ሊጠቀሱ ይችላሉ።

ሙሴ ፎርዖን ባወጀው ሕግ መሠረት እንዳይገደል ብላ እናቱ ከቄጠማ በተሠራ ሳጥን ውስጥ አድርጋ በጥቁር አባይ ወንዝ ዳሪቻ እንዳስቀመጠችውና የግብጽ ልዕልት አግኝታው እንዳሳደገችው በኦሪት ዘጸአት ምዕራፍ ፪ ላይ እናገኛለን። እንዲሁም በሮማውያን ተረት መሠረት የሮማ ከተማ መሥራች ናቸው የሚባሉ ሁለት መንትየ ወንድማሞች አባታቸውን የገደለ ጠላት (አጎታቸው) እንዳይገድላቸው ብላ እናታቸው በቅርጫት ውስጥ አስገብታ የሮማ ከተማን በሁለት ላይ ሰንጥቆ በሚፈሰው ጢበርዮስ በተባለ ወንዝ ላይ እንዲንሳፈፉ አድርጋ አስቀመጠቻቸው፣ በኋላ ሕፃናቶቹን የያዘ ቅርጫት ወደ ወንዙ ዳሪቻ ተጠጋና ከዛው አንዲት ተኵላ ወስዳ በወተትዋ አሳደገቻቸው ይላል። የላስታ ሥርወ-መንግሥት ጀማሪ አፄ መራ ተክለሃይማኖት ባለቤት ንግሥት መሶበወርቅም ከወርቅ በተሠራ መሶብ ውስጥ ተዘግታ ከወራጅ ውሃ ተጥላ እንደነበረች፣ በኋላ ግን ውሃው ወደ መንገድ እንደተፋትና ከዛ በአከባቢው የነበሩ ሰዎች ወስደው እንዳሳደጓት ይተረካል።

ያም ሆነ ይህ ዋና ቁምነገር በተረቱ ውስጥ የተካተቱ ዝርዝሮች ሳይሆን ተረቱ በእውነት ላይ የተመሠረተ ይመስላል ወይ የሚለው መሆን አለበት። ለምሳሌ አፄ ይትባረክ ሸፍቶበት ነበር በተባለው አከባቢ ተንቀሳቅሶ እንደሆነ በሚገባ መመርመር በጣም አስፈላጊ ነው። ምክንያቱም እዛ አከባቢ ኖሮ ከሆነ በአከባቢው ካገኛት ሴት ልጅ ሊወልድ ይችላል። እና ይህንን ታሪክ የሚደግፉ ፍንጮች ወይም መረጃዎች ካሉ ማጥናት አስፈላጊ ይመስለኛል። ስለሆነም ወደፊት ለሚደረጉ ጥናቶች መነሻ እንዲሆንና ወጣቱ ትወልድ የራሱን ታሪክ በአገባቡ እንዲያጠናና እንዲመረምር ለማነሳሳት ያስችላሉ የምላቸው አንዳንድ ነጥቦችን ነካክቼ ማለፍ እፈልጋለሁ።

ስለ ላስታ ነገሥታት የዘር ሐረግና የቅዱስ ይምርሃነ ክርስቶስ፣ የቅዱስ ገብረማርያም፣ የቅዱስ ላሊበላና የቅዱስ ነአኩቶ-ለአብ ታሪክ የፃፉት ዲ/ን ፈንታ ታደሰ አፄ ይትባረክ የላሰታ ሥርወ-መንግሥት የመጨረሻ ንጉሥ እንደነበረና ከዚህ በኋላ የላስታ ንጉሣዊ ቤተሰብ ምድረ ላስታን ለቆ ወደሌላ ሃገር እንደተሰናበቱ ይገልፃሉ። ወዴት እንደሆነ ግን ደራሲው አላብራሩም። ወደ ዓጋመ/ጉንዳጉንደ አከባቢ ይሆን?

**ኮንቲ ሮሲኒ ‘የኢትዮጵያ ታሪክ’ (Storia D’Etiopia) በሚል ርእስ በጻፈው በታሪክ ሊቃውንት ከፍተኛ እውቅና ያገኘ መጽሐፍ ውስጥ አጼ ይኩኖ-አምላክ የኢትዮጵያ ንጉሥ መሆኑን ባወጀ ጊዜ (የኢትዮጵያ ንግሥና ከዛጕው ሥርወ-መንግሥት ሰሎሞናዊ ወደ ሚባለው ሥርወ-መንግሥት የተላለፈበት ጊዜ መሆኑ ነው) ማኽል አገር ውስጥ የተሸነፉ ዛጕየዎች ትግላቸውን ለተወሰነ ጊዜ በሰሜን ኢትዮጵያ ከዓፋር መሬት በስተሰሜን በሚገኝ ተራራማ አከባቢ ቀጥሏል፤ ይህም የኢሮበ አፈታሪክ ስለ ንጉሥ ይትባረክ በዚሁ አከባቢ ሸፍቶ እንደነበረ የሚተርከውን ይደግፋል ይላል (ገፅ 317)።**

አፄ ይትባረክ ይሁን ሌላ አንድ ባለስልጣን በዛ አከባቢ ሸፍቶ እንደነበረ የሚያሳዩ ምልክቶች አሉ። ስለዚህ አፈታሪኩ መሠረት ያለው ሊሆን ይችላል።

**ኮንቲ ሮሲኒ በ1260 አከባቢ አንድ የአገው ስም ያለው ደላንዳ የሚባል የንጉሥ ማዕረግ ያለው ሹም በዛ አከባቢ እንደነበረ ይታወቃል ይላል።ባለሥልጣኑን ይርደአነክርሰቶስ የሚባል ከአፄ ላሊበላ ዘመን ጀምሮ የደብረ-ሊባኖሰ (ሽመጃና) ገዳም አበምኔት የነበረ ሰው ከሰባት ልጆቹ ጋር፣ በዛን ዓመት ውሰጥ ለገዳሙ ስጦታ አድርጎ የነበረው ምስለነ-እግዝእ ወይም ሓሪዛይ የሚባል የደብሪ-ማዕዖ ገዢ የመሳሰሉ ሰዎች ይደግፉት እንደነበረም አብራርቷል። ኮንቲ ሮሲኒ የዛጕ ሥርወ-መንግሥት በ”ሰሎሞናዊ” ሥርወ-መንግሥት ከተወሰደ በኋላ የዛጕ/የአገው ነገዶች በብዛት ወደ**

ሰሜን ኢትዮጵያ እንደፈለሱም ጽፏል። ታዋቂዉ የታሪክ ሊቅ ኮንቲ ሮሲኒ የመዘገባቸው ነጥቦች የኢሮብ ቅድመ-አያቶችን ከላስታ ነገሥታት ጋር የሚያያይዘው አፈ-ታሪክን የሚደግፉ ይመስላል።

በዚሁ መጣጥፍ በክፍል አንድ ነጋዴዎች ያ በወንዝ የተጣለ ሕፃን ባገኙ ጊዜ የነጋዴዎቹ መሪ ልጁን "ለንጉሡ ሰጠው፤ በዚያም አደገ፣ ንጉሡም እጅግ ይወደው ነበረና ሹመትና ብዙ ባለመዋልነት አገኘ...ሲሞትም ሣለ አልጋ ለሱ ሰጠው" ይላል። ሕፃኑ የተሰጠው ንጉሥ ያ በኮንቲ ሮሲኒ የተጠቀሰው ደላንዳ ይሆን? መቸም በዛን ጊዜ በዛ አከባቢ ነበረ የተባለው ደላንዳ ብቻ ነው፤ ይትባረክ ግን በሕወት የነበረ አይመስልም፤ ቢኖር በብዙ ጥረትና ምኞት የወለደውን ልጅ በወሰደ ነበርና። ንጉሡ "ሲሞት አልጋ ለሱ ሰጠው" የተባለውስ? መቸም ወረደ-ምሕረት ንጉሥ እንደነበረ ነው የሚነገረው። ንግሥናውን ያገኘው እውነትም በዚህ መልክ ይሆን? ንጉሥ ወረደ-ምሕረት ቡልድም የምትባል የሐረዛይ ልጅ አግብቶ ሰንበታይን ሱመንና ሓናከን እንደወለደ የኢሮብ አፈ-ታሪክ ይተርካል። በኮንቲ ሮሲኒ የተጠቀሰው ሓሪዛይ እሱ ይሆን?

መጣጥፉን ጥያቄዎችን በማቅረብ የደመደምኩት ሆን ብዬ ሌሎች የኢሮብ ምሁራን ትኩረት እንዲያደርጉበትና ጥናቱን እንዲቀጥሉበት ብዬ ነው። በተለይ በኮለጆች ውስጥ የታሪክ ትምህርት በዋናነት የሚያጠኑ ተማሪዎች በዘዴ የተከናወነ ጥናት እንዲያደርጉበት እየጋበዝኩ ይህንን ክፍል እዚህ እደመድመዋለሁ።

## <u>ተጨማሪ</u>

### <u>ቋንቋና የሰዉ የተፀውዖ ስም፦</u>

የኢሮብ ቅድመ-አያቶች ትግርኛ ተናጋሪ ትግራያውያን ነበሩ፣ አሁን የኢሮብ ህዝብ ወደሚኖርበት አከባቢ ከመጡ በኋላ በአከባቢው ከቆዩ ህዝቦች የሳሆ ቋንቋ ተምረዋል የሚል አባባል ይደጋገማል። ሆኖም ይህ አባባል በደንብ በጥናት ላይ የተመረኰዘ ሳይሆን በቀላል ሎጂክ ላይ የተመሠረተ ይመስላል። ሎጂኩን እንደሚከተለው ማስቀመጥ ይቻላል።

የኢሮብ ቅድመ አያት (ወረደ-ምሕረት) መጀመርያ በክልተ-አውላዕሎ አከባቢ ይኖር ነበር።
በክልተ አውላዕሎ አከባቢ የሚኖር ህዝብ የትግርኛ ቋንቋ ይናገራል (ዛሬ)
ስለዚህ የኢሮብ ቅድመ-አያቶች ትግርኛ ተናጋሪ ነበሩ።

ላየኛውን አባባል እንደ እውነተኛ ታሪክ ከተቀበሉ በኋላ የሚቀጥለው ሌላ አባባል ደግሞ እንደሚከተለው ማስቀመጥ ይቻላል፦

የኢሮብ ህዝብ ቅድመ-አያቶች ትግርኛ ተናጋሪ ነበሩ፤
አሁን የኢሮብ ህዝብ ጎረቤቶቹ የሚናገሩትን የሳሆ ቋንቋ ይናገራል፤
ስለዚህ ኢሮቦች የሳሆ ቋንቋ የተማሩት ባከባቢው ከቆየው ሳሆ ተናጋሪ ህዝብ መሆን አለበት።

እዚህ ላይ ያየናቸው አባባሎች በሌላ ማስረጃ እስካልተደገፉ ድረስ ጥልቀት የሌላቸው ተራ ግምቶች ናቸው። ለመሆኑ የኢሮብ ቅድመ-አያቶች ትግርኛ ይናገሩ እንደነበረ የሚያሳይ ምን ማስረጃ አለ? ከዳህላክ ደሴቶችና ከምጽዋ እስከ ጅቡቲ በሚደርሰው በምሥራቃዊ የአፍሪካ ቀንድ የሚነገሩ አፋርኛና ሌሎች ኩሻዊ ቋንቋዎች ለምን በግምት ውስጥ አልገቡም? ምናልባት የሳሆ ቋንቋ ትግርኛ እየተሰፋፋ ከመሄዱ በፊት ክልተ-አውላዕሎን ጨምሮ ሰፋ ባለ ጀዮግራፊያዊ አከባቢ ይነገር የነበረ ቋንቋ ሊሆን ይችላል የሚል አስተሳሰብ በግምት ውስጥ ለምን አልገባም? ሌለኛውም ግምት ብቻ ነውና። የሳሆ ቋንቋ ያኔም አሁን በሚነገርበት አከባቢ ብቻ የተወሰነ እንደነበረ ተደርጎ

የሚወሰደው በምን ማስረጃ ላይ በመመርኮዝ ነው? ሄንሪ ሶልት (Henry Salt) የተባለ ደራሲ በአሥራ ዘጠነኛ ክፍለ-ዘመን መጀመርያ ብዙ የኢትዮጵያ ክፍለ ግዛቶችን ጎበኝቶ በፃፈው መጽሓፉ አንዳንድ ባገርቷ የሚነገሩ ኩሻዊ ቋንቋዎች እንደሚመሳሰሉ በሚያሳይበት መዕራፍ ውስጥ ያኔ በሃረር አከባቢ ይነገር የነበረ የአዳል ቋንቋ ከሳሆ ጋር በጣም ተመሳሳይ እንደነበረ በሁለቱም ቋንቋዎች የሚገኙ ቃሎች እያስተያየ ጽፏል። አሁንም ቢሆን በጂቡቲና ሃረር አከባቢ ዳርዳሩ ላይ የሚነገረው ቋንቋ ከሳሆ ጋር መጣም ይመሳሰላል። በሲዳማና በሌሎች የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ውስጥ ሳይቀር አልፎ-አልፎ የሳሆ ቋንቋ ቃሎችና ሃረጎች ይገኙባቿል፡፡ ወደ ምሥራቃዊ ትግራይ መለስ ብለን ስናይ ከሳዕሲዕ እስከ ክልተ-አውላዕሎ ባለው ረጂም ጀዮግራፊያዊ ቀጠና የሚገኙ መንደሮች ስሞች የሳሆ ትርጉም ያላቸው ናቸው ዛሬ በነዚህ መንደሮች የሚኖሩ ሰዎች የሚናገሩት ቋንቋ ግን ትግርኛ ነው። ይህ ሁሉ የሚያሳየው ሳሆ ከጥንት የቆየ ሰፊ ቋንቋ እንደነበረና በኋላ የኢትዮጵያ ትልልቅ ቋንቋዎች የሚናገሩ ጎሳዎች እየተስፋፉ በሄዱ መጠን የሳሆ ተናጋሪ ህዝብ ኩታ-ገጠም ወዳልሆኑ የተለያዩ ጀዮግራፊያዊ ቀጠናዎች እየተቆራረጠ እንደሄደ ወይም ህዝቡ እየተዋሃደ እና ቋንቋውም እየተዋጠ/እየጠፋ ሂዶ ሊሆን እንደሚችል ግምት ውስጥ መግባት አለበት። ስለዚህ ዛሬ ባንድ ወገን የኢሮብ አጐራባች የሆነ ህዝብ ሳሆ ይናገራልና ኢሮቦች ቋንቋውን የተማሩት ከነሱ መሆን አለበት የሚል በደንብ ያልተጠና ተራ ግምት ሲሰጥ የኢሮብ ቅድመ-አያቶች ከጥንትም ቢሆን የሳሆ ወይም ተመሳሳይ 'ኩሻዊ' ቋንቋ ተነጋሪ የነበሩ ሊሆኑ ይችላሉ የሚል አስተሳሰብ ከግምት ውስጥ ለምን አልገባም?

የኢሮብ ቅድመ-አያቶች አሁን የኢሮብ ሕዝብ ወደሚኖርበት መሬት የመጡት ከክልተ-አውላዕሎ (ኦላዕሎ?) መሆኑ የማይስማሙበት ወገኖች ቢኖሩም አባባሉን እንደእውነት ተቀብለን ብንነሳ ሌላ መመለስ ያለበት ጥያቄ ሊቀርብ ይችላል። ለመሆኑ ያኔ ማለት ከሰባት መቶ ዓመታት በፊት በክልተ-አውላዕሎ አከባቢ ይነገር የነበረ ቋንቋ ትግርኛ ለመሆኑ ምን ማስረጃ አለን? መቸም የትግርኛ ቋንቋ ከምዕራብ ወደ ምሥራቅ እየተስፋፋ መሄዱ የማይካድ ሐቅ ነው። እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ትግራይ ተብሎ ሲጠራ የነበረውም ያው የትግርኛ ቋንቋ መሠረት የነበረ አከባቢ ነው እንጂ በዛሬው ትግራይ የሚገኙት ዞባዎች፣ አውራጃዎችና ወረዳዎችን ሁሉ ያጠቃለለ ስም አልነበረም። እና ያኔ በክልተ-አውላዕሎ አከባቢ ይነገር የነበረ ቋንቋ ሳሆ፣ አፋር ወይም ሌላ ተመሳሳይ ኩሻዊ ቋንቋ ኖሮ በኋላ የትግርኛ ቋንቋ የበላይነት እያገኘ ሂዶ እንደሆነስ? ይህ አዝማሚያ አሁንም በፍጥነት እየቀጠለ ነው። በኛ ዕድሜ እንኳን ሳይቀር ብዙ ለውጥ ተደረጓል። ለምሳሌ ከአርባና አምሳ ዓመታት በፊት አብላጫው የኢሮብ ህዝብ ትግርኛ ፈጽሞ አያውቅም ነበር። አሁን ግን ተቃራኒው እውነት ሊሆን ይችላል።

የኢሮብ ቅድመ-አያቶች የተፀውዖ ስሞችን ስንመለከትስ የትግርኛ የተፀውዖ ስም ነው የምናገኘው? ስማቸው ትግርኛ ተናጋሪ እንደነበሩ ነው የሚያመለክተው? የሚሉ ጥያቄዎች መልስ የሚሹ ናቸው። እስኪ ከሔባይ ጀምረን ወደታች እየሄድን እንየው። የዘር ሐረግ አወራረድ አንድ ወጥ በሆነ መልክ ባይሆንም ከሔባይ በላይም ይሄዳል ሆኖም ከዛ በላይ ያለው በጣም አጠያያቂ ስለሆነ ለጊዜው ከሱ በታች ባለው እናተኵር። (ለነገሩማ እውነት ይሁን አይሁን ከዛ በላይ በሚጠቀሰው የዘር አወራረድ ውስጥም ቢሆን የትግርኛ ስም አይገኝበትም) የሆነ-ሆኖ ሔባይ(ሔርባይ?) አይፋራሕ፣ ዓሚዶ፣ ወረደ-ምሕረት፣ ሰንበታይ፣ ሓናከ፣ ሱመ፣ ሱባይቶ፣ ያትኪ፣ ጋለባ(ጋሎባ)፣ አፍጋራ፣ ሲፋሪ፣ አፍራሃ፣ ረዳኩም፣ ሓሳባላ፣ ሱባጋዲስ፣ ኩማኒት፤... ሱባልሳ፣ ጋይሶላ፣ ሓይዲቢድ፣ አድጋዳ፣ አፍራሓ፣... ቡክናይታ፣ ጋፋዕታ፣ ዓንዳድ-ኩማኒት... ወዘተ. ስንመለከት የግዕዝ ስም ያለው ከወረደ-ምሕረት በስተቀር ከሱ በፊትም ሆነ ከሱ በኋላ በቀደምት የኢሮብ አበው አንድ የትግርኛ ስም ያለው አናገኝም። በኢሮብ ውስጥ የትግርኛ ስሞች የምናገኘው ከብዙ ትወልድ በኋላ ነው

*አሁን ደግሞ ሙሉ በሙሉ የትግርኛ እየሆነ ሂደዋል፤ ይህ የሚያሳየው ደግሞ ኢሮቦች ፊት ትግርኛ ተናጋሪ እንደነበሩ ሳይሆን የትግርኛ ባህልና ቋንቋ በኋላ ወደዛ አከባቢ እንደተስፋፋና ቀስበቀስ የበላይነትን እየያዘ እንደሄደ ነው።*

*ኮንቲ ሮሲኒ ስለ የወረደ-ምሕረት ልጆች የሚከተለውን ጽፏል። በደቡባዊ ትግራይ ከሚገኘው ከወንበርታ እስከ ከመረብ ወንዝ በስተምዕራብ በሚገኝ አከባቢ በሰፊ መሬት የሠፈረው ህዝብ በመሠረቱ የሳሆ ሕዝብ ነው። ሆኖም በሰሜናዊ ምሥራቅ ዓጋመ ከሚኖሩ ኢሮቦች በስተቀር ሌሎች ቋንቋቸውን፣ ባህላቸውን፣ ማህበራዊና ሥነ-ቊጠባዊ ስልት፣ ፖለቲካዊ አስተዳደር ወዘተ. በሙሉ አብሮዋቸው በሚኖሩ በአበሾች ቋንቋና ባህል ተክተውታል ይላል (አል ራጋሲ ገፅ 47)። ይህ አባባል የወረደ-ምሕረት ልጆች መጀመርያ ትግርኛ ተናጋሪ እንደነበሩ ሳይሆን ተቃራኒውን ነው የሚያሳየው። ለወረደ-ምሕረት ብቻ ለምን የግዕዝ ስም ተሰጠ? ዘውድ ሲጭን ቤተክርስቲያን የሰጠችው የንግሥና ስሙ ይሁን? መቸም ንጉሥ እንደነበረ ደጋግሞ ተነግሯል፤ እውነት ሊሆንም ይችላል። በተረት መልክ ቢሆንም ይህ ስም የተሰጠው በኋላ እንደሆነ በአፈ-ታሪኩ ውስጥም ተነግሯል ። በኢትዮጵያ ረጂም ታሪክ ውስጥ በአንድ ንጉሠ-ነገሥት ሥር በየአከባቢ የተሾሙ ብዙ ነገሥታት እንደነበሩ የታወቀ ነው። ለምሳሌ ግራ(ሃ)ም ሀንኮክ የተባለ ጸሓፊ ስለ ጽላተ ሙሴ በፃፈው መጽሐፉ ውስጥ አፄ ላሊበላ ንጉሠ ነገሥት የነበረበት ጊዜ ከሱ በታች በአገሪቷ ውስጥ 35 ነገሥታት እንደነበሩ ጽፏል። ስለዚህ ወረደምሕረት ንጉሥ ነበረ ሲባል የማይቻል ነገር ሆኖ መታየት የለበትም።*

*ኮንቲ ሮሲኒ እዚህ ላይ የተጠቀሰው ስለ ወረደ-ምሕረት ልጆች ያለውን የፃፈው ከመቶ ዓመታት በፊት ነው፤ እንኳን ያኔ ከአርባ ዓመታት በፊትም ሁኔታው የተለየ እንደነበረ ከላይ ባጭሩ ለማሳየት ሞክሬያለሁ። የጥንቱ የሆነ ሆኖ ዛሬ የኢሮብ ህዝብ ቋንቋና ባህል በሚያስፈራ ሁኔታ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጠፋ ስለመሆኑ ምንም የሚያከራክር አይደለም። ስለሆነም የጥንቱ ታሪካችንን በትክክል እየጻፍን ዛሬ በመጥፋት ላይ ያለውን ቋንቋችንና ባህላችን ፈጽሞ ከመጥፋቱ በፊት ለማዳን የተባበረ ጥረት ማድረግ ይኖርብናል እላለሁ። በዚህ መሰረትም ይህን አጋጣሚ በመጠቀም ለኢሮብ ቋንቋና ባህል ኮሚቴ ጠንክሩ አይዙዋችሁ ለማለትና ሥራችው ስኬታማ እንዲሆን እንደምመኝም ለመግለጽ እወዳለሁ።*

---

<u>አስ፡-</u>

ስለማንኛው ነገር ሲነገር ወይም ሲጻፍ በአሃዝ አብላጫ የሆነውን ይዘህ ነው እንጂ የተነገረ ወይም የተጻፈ ሁሉንም ያጠቃልላል ማለት አይደለም። ለምሳሌ የትግራይ ህዝብ ቋንቋ ትግርኛ ነው ሲባል አብዛኛው የትግራይ ሕዝብ የሚናገረውን ቋንቋ ለማመልከት ነው እንጂ ሌላ በትግራይ ውስጥ የሚነገር ቋንቋ ፈፅሞ የለም ለማለት አይደለም። በተጨባጭ የሳሆ፣ የኩናማ የአማርኛ...ቋንቋዎች በትግራይ ውስጥ ይነገራሉ። እንዲሁም የኢሮብ ሕዝብ የትውልድ ሓረግ ሲነገርና የኢሮብ ሕዝብ ቅድመ-አያት ወረደ-ምሕረት ነው ወይም ሱመ ነው ሲባል ስለ አብዛኛው ነው እንጂ ዛሬ በኢሮብ መሬት ያለው ሁሉ ከጥንት ጀምሮ ሙሉ በሙሉ የወረደ-ምሕረት ወይም የሱመ ልጆች ናቸው ማለት አይደለም። ከጥንት ጀምሮ ሲወርድሲዋረድ የመጣ የዘር ሐረግ ሲታይ አሁን ኢሮብ የሚባል ህዝብ ከሱመ ልጆች በተጨማሪ የካያይታ፣ የጋዓሶ፣ የሓዞ፣ የዳብሪመላ፣ የሱሩክሶ ወዘተ. ተወላጆችን ያጠቃልላል። ሆኖም ግን ያለንበት ጊዜ በኢሮብ ምድር የሚኖር የሱመ ዝርያ የሌለው ሰው የለም ለማለት ይቻላል። እንኳን በኢሮብ ውስጥ በመላ የዓጋመና የሽመጃና አከባቢ/ሪጀን እንኳ ባንድ ወይም በሌላ መልኩ የኢሮብ ዘር የሌለበት ካለ በጣም የተወሰነ ነው የሚሆነው።

---

*ሚያዚያ* 2003